USDA Food and Nutrition Service
U.S. DEPARTMENT OF AGRICULTURE

# ለነፃ እና ለቅናሽ ዋጋ የትምህርት ቤት ምግብ እንዴት ማመልከት እንደሚቻል

የነጻ እና የቅናሽ ዋጋ የትምህርት ቤት ምግቦችን ማመልከቻ ለመሙላት እንዲረዳዎት እባክዎ እነዚህን መመሪያዎች ይጠቀሙ። **ምንም እንኳን ልጆቻችሁ ውስጥ ከአንድ በላይ ትምህርት ቤት ውስጥ ቢማሩም** ለአንድ ቤተሰብ አንድ ማመልከቻ ብቻ ማስገባት ያስፈልጋል። [Insert School District here].

ማመልከቻው የልጅዎን(ጆችዎን) ለነጻ ወይም ለቅናሽ ዋጋ የትምህርት ቤት ምግቦች ብቁነት ለመወሰን ሙሉ በሙሉ መሞላት አለበት። እባክዎን እነዚህን መመሪያዎች በቅደም ተከተል ይከተሉ! እያንዳንዱ የመመሪያው ደረጃ በማመልከቻው ላይ ካሉት ደረጃዎች ጋር ተመሳሳይ ነው። በማንኛውም ጊዜ ቀጥሎ ምን ማድረግ እንዳለብዎት እርግጠኛ ካልሆኑ፣ እባክዎን [Insert School/School District contact here; phone and email preferred]. ላይ ያነጋግሩ።

**ማመልከቻውን በሚሞሉበት ጊዜ እባክዎን እስክሪብቶ (እርሳስ ሳይሆን) ይጠቀሙ እና በግልጽ ለማተም የተቻለዎትን ያድርጉ።**

## ደረጃ 1፦ እስከ እና 12ኛ ክፍልን ጨምሮ <u>ሁሉንም</u> ልጆች፣ ህፃናት እና ተማሪዎችን ይዘርዝሩ

በቤተሰባችሁ ውስጥ ምን ያህል ሕጻናት፣ ትምህርት ቤት ያልገቡ ልጆች፣ እና የመጀመሪያ ደረጃ/መካከለኛ/ሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች እንደሚኖሩ ይንገሩን። የቤተሰብዎ አካል ለመሆን ከእርስዎ ጋር ዝምድና ሊኖራቸው አይገባም።

**እዚህ ማንን ልዘርዝር?** ይህንን ክፍል በሚሞሉበት ጊዜ፣ እባክዎን እንደሚከተሉት ያሉ በቤተሰብዎ ውስጥ ያሉትን ሁሉንም አባላት ያካትቱ፦

- ዕድሜያቸው 18 ወይም ከዚያ በታች የሆኑ እና በቤተሰቡ ገቢ የሚደገፉ ልጆች፤
- በእርስዎ እንክብካቤ ውስጥ በፍርድ ቤት ወይም በግዛት/አካባቢ ኤጀንሲ በኩል በመደበኛ የማደጎ ዝግጅት ስር የሆኑ፣ ወይም እንደ ቤት አልባ፣ ስደተኛ ወይም የሸሸ ወጣት ብቁ የሆኑ፤
- (<u>እድሜ ምንም ይሁን ምን</u>) [Insert School/School system here]. የሚማሩ ልጆች።

| | | | |
|---|---|---|---|
| **A) የእያንዳንዱን ልጅ ስም ይዘርዝሩ።** የእያንዳንዱን ልጅ ስም ያትሙ። ለእያንዳንዱ ልጅ ማመልከቻ አንድ መስመር ይጠቀሙ። ስሞችን በሚያትሙበት ጊዜ፤ በእያንዳንዱ ሳጥን ውስጥ አንድ ፊደል ይጻፉ። ቦታ ካለቀ ያቁሙ። በማመልከቻው ላይ ከተሰጠው መስመሮች ይልቅ ብዙ ልጆች ካሉ፣ ለተጨማሪ ልጆች ከሚያስፈልጉት መረጃዎች ጋር ሁለተኛ ወረቀት (ወይም በኤሌክትሮኒክ መንገድ ከሞሉ ሁለተኛ ማመልከቻ) ያያይዙ። ይህ በደረጃ 3 ላይ ለአዋቂዎችም ተግባራዊ ይሆናል። "MI" የአባት ስም የመጀመሪያ ፊደል አጭር ምህጻረ ቃል ነው። የእያንዳንዱን ልጅ የአባት ስም የመጀመሪያ ፊደል በሳጥኑ ውስጥ ያትሙ። | **B) ልጁ ተማሪ ነው?** “አዎ” ከሆነ፣ የተማሪውን የክፍል ደረጃ በቀኝ በኩል ባለው “ክፍል” የሚለው አምድ ላይ ይፃፉ። | **C) *Foster Child* አሉዎት?** የተዘረዘሩት ልጆች *Foster Child* ከሆኑ፣ ከልጁ ስም ቀጥሎ ባለው “*Foster Child*” በሚለው ሳጥን ላይ ምልክት ያድርጉ። ለ*Foster Child* ብቻ የሚያመለክቱ ከሆነ፣ **ደረጃ 1** ከጨረሱ በኋላ፣ ወደ **ደረጃ 4** ይሂዱ።<br><br><u>ከእርስዎ ጋር የሚኖሩ *Foster Child* እንደ ቤተሰብዎ አባላት ሊቆጠሩ ይችላሉ እና በማመልከቻዎ ላይ መዘርዘር አለባቸው</u>። የሚያመለክቱት ለሁለቱም ለ*Foster Child* እና የማደጎ ላልሆኑ ልጆች ከሆነ፣ ወደ ደረጃ 3 ይሂዱ። ማስታወሻ፦ የጉዲፈቻ ልጆች እንደ *Foster Child* አይቆጠሩም። *Foster Child* ትንሽ ልጅ ሲሆን በግዛት ጥበቃ ተወስዶ በወላጅ ወይም በአሳዳጊው ምትክ ልጁን የሚንከባከብ በመንግስት ፈቃድ ያለው ጎልማሳ ጋር የተቀመጠ ልጅ ነው። | **D) ቤት የሌላቸው፣ ስደተኛ ወይም የሸሹ ልጆች አሉ?** በዚህ ክፍል ውስጥ የተዘረዘረው ማንኛውም ልጅ ይህንን መግለጫ ያሟላል ብለው ካመኑ፣ ከልጁ ስም ቀጥሎ ባለው "ቤት አልባ፣ ስደተኛ፣ የሸሸ" የሚለው ሳጥን ላይ ምልክት ያድርጉ እና <u>ሁሉንም የማመልከቻውን ደረጃዎች ይሙሉ</u>። ቤት አልባ፣ ስደተኛ፣ የሸሸ <u>ሁኔታ ከሚመለከታቸው የፕሮግራም ሰራተኞች ጋር መረጋገጥ አለበት</u>። የትምህርት ቤቱ ወረዳ የእርስዎን የተማሪ ቤት አልባ፣ ስደተኝነት ወይም የመሸሽ ሁኔታ ማረጋገጥ ካልቻለ፣ በገቢ ላይ የተመሰረተ ማመልከቻ እንዲሞሉ የትምህርት ቤቱ ወረዳ ያነጋግርዎታል። <u>የትምህርት ቤቱ ወረዳ በኋላ ላይ እርስዎን ማነጋገር እንዳይጠበቅበት ለመከላከል አሁን የገቢ መረጃ ለማቅረብ መምረጥ</u> ይችላሉ። |

*ይህ ተቋም የእኩል ዕድል አቅራቢ ነው።*

## ደረጃ 2 SNAP፣ TANF ወይም FDPIR ውስጥ ይሳተፋሉ?

**ከዚህ በታች በተዘረዘሩት የእርዳታ ፕሮግራሞች ውስጥ በቤተሰብዎ ውስጥ ያለ ማንም ሰው (እርስዎን ጨምሮ) በአሁኑ ጊዜ የሚሳተፉ ከሆነ፣ ልጆችዎ ለነጻ የትምህርት ቤት ምግብ ብቁ ይሆናሉ፦**

- ተጨማሪ የተመጣጠነ ምግብ እርዳታ ፕሮግራም (Supplemental Nutrition Assistance Program, SNAP) ወይም [Insert State SNAP here].
- ጊዜያዊ እርዳታ ለተቸገሩ ቤተሰቦች (Temporary Assistance for Needy Families, TANF) ወይም [Insert State TANF here].
- በህንድ የተያዙ ቦታዎች ላይ የምግብ ስርጭት ፕሮግራም (Food Distribution Program on Indian Reservations, FDPIR)።

| A) ከላይ በተዘረዘሩት ፕሮግራሞች ውስጥ ከቤተሰብዎ ውስጥ ማንም የማይሳተፍ ከሆነ፦ | B) ከላይ በተዘረዘሩት ፕሮግራሞች ውስጥ ከቤተሰብዎ ውስጥ ማንም የሚሳተፍ ከሆነ፦ |
|---|---|
| • **ደረጃ 2** ዉስጥ "አይ" የሚለውን ያመልክቱ እና ወደ **ደረጃ 3 ይሂዱ።** | • ለSNAP፣ TANF ወይም FDPIR የጉዳይ ቁጥር ይጻፉ። አንድ የጉዳይ ቁጥር ብቻ ነው ማቅረብ ያለብዎት። ከእነዚህ ፕሮግራሞች በአንዱ ውስጥ ከተሳተፉ እና የጉዳይ ቁጥርዎን ካላወቁ፣ የሚከተለውን ያነጋግሩ፦<br>[Insert State/local agency contacts here].<br>• ወደ **ደረጃ 4** ይሂዱ። |

## ደረጃ 3፦ ለእያንዳንዱ አባል ሁሉንም የቤተሰብ አባላት እና ገቢ ይዘርዝሩ

**ገቢዬን እንዴት ሪፖርት አደርጋለሁ?**

- ቤተሰብዎ ሪፖርት የሚደረግ ገቢ እንዳለው ለማወቅ በማመልከቻ ቅጹ ጀርባ ላይ "**<u>የገቢ ምንጮች</u>**" እና "**<u>ለልጆች የገቢ ምሳሌዎች፣</u>**" የሚል ርዕስ ያላቸውን ዝርዝሮች ይጠቀሙ።
- ሁሉንም መጠኖች በጠቅላላ ገቢ ብቻ ሪፖርት ያድርጉ። ሁሉንም ገቢ በሙሉ ዶላር ሪፖርት ያድርጉ። ሳንቲሞችን አያካትቱ።
  - ጠቅላላ ገቢ ማለት ከታክስ እና ተቀናሾች **በፊት** የተቀበለው ጠቅላላ ገቢ ነው።
  - ብዙ ሰዎች ገቢ "ወደ ቤት የሚወስዱት" መጠን እንጂ አጠቃላይ "ጠቅላላ" መጠን አይደለም ብለው ያስባሉ። በዚህ ማመልከቻ ላይ ሪፖርት የሚያደርጉት ገቢ ለግብር፣ ለኢንሹራንስ አረቦን ወይም ከክፍያዎ ለሚወሰዱ ሌሎች መጠኖች እንዳልተቀነሰ ያረጋግጡ።
- ሪፖርት ለማድረግ ምንም ገቢ በሌለበት በማንኛውም መስክ ላይ "0" ይጻፉ። ባዶ የሚተዉ የገቢ መስኮች በሙሉ እንደ ዜሮ ይቆጠራሉ። "0" ብለው ከጻፉ ወይም ማንኛውንም መስክ ባዶ ከተዉ፣ ሪፖርት ለማድረግ ምንም ገቢ እንደሌለ እያረጋገጡ (ተስፋ እየሰጡ) ነው። የአካባቢው ባለስልጣናት የቤተሰብዎ ገቢ በስህተት ሪፖርት ተደርጓል ብለው ከጠረጠሩ፣ ማመልከቻዎ ይመረመራል።
- በእያንዳንዱ መስክ በስተቀኝ ያሉትን አመልካች ሳጥኖቹን በመጠቀም እያንዳንዱን የገቢ አይነት በምን ያህል ጊዜ እንደሚቀበሉ ምልክት ያድርጉ።

### 3.A. በአዋቂዎች የተገኘውን ገቢ ሪፖርት ያድርጉ

**እዚህ ማንን ልዘርዝር?**

- ይህንን ክፍል በሚሞሉበት ጊዜ፣ እባክዎን ከእርስዎ ጋር የሚኖሩ እና ገቢ እና ወጪ የሚጋሩ በእርስዎ ቤተሰብ ውስጥ ያሉ ሁሉንም የጎልማሶች አባላት ያካትቱ፣ <u>ምንም እንኳን ዘመድ ባይሆኑም እና የራሳቸው ገቢ ባይኖራቸውም</u>።
- ***የሚከተሉትን እንዳያካትቱ፦***
  - ከእርስዎ ጋር የሚኖሩ ነገር ግን በቤተሰብዎ ገቢ የማይደገፉ እና ለቤተሰብዎ ገቢ የማያዋጡ ሰዎች።
  - አስቀድሞ **ደረጃ 1** ላይ የተዘረዘሩ ሕፃናት፣ ልጆች እና ተማሪዎች።

## ደረጃ 3፡- ሁሉንም የቤተሰብ አባላት እና ገቢ ለእያንዳንዱ አባል ይዘርዝሩ

**1) የአዋቂዎች ቤተሰብ አባላትን ስም ይዘርዝሩ።**
የእያንዳንዱን የቤተሰብ አባል ስም "የአዋቂዎች ቤተሰብ (የመጀመሪያ እና የመጨረሻ) ስሞች" የሚል ምልክት በተደረገባቸው ሣጥኖች ውስጥ ያትሙ። የኮሌጅ ተማሪዎችን ያካትቱ፣ በግብር ላይ ራሳቸውን ችለው እስኪልታወቁ ድረስ (ሁሉም የኮሌጅ ተማሪዎች እንደ ትልቅ ሰው ይቆጠራሉ)። **ደረጃ 1** ላይ <u>የዘረዘሯቸውን የቤተሰብ አባላትን አይዘረዝሩ</u>።

**2) ከስራ የሚገኘውን ገቢ ይዘርዝሩ።**
በማመልከቻው ላይ "ከስራ የሚገኝ ገቢ" በሚለው መስክ ውስጥ ከስራ የሚገኘውን ገቢ ሁሉ ይዘርዝሩ። ይህ አብዛኛውን ጊዜ በሥራ ላይ ከመሥራት የሚቀበሉት ገንዘብ ነው። ራስዎን የሚያስተዳድሩ የንግድ ወይም የእርሻ ባለቤት ከሆኑ፣ የእርስዎን የተጣራ ገቢ ሪፖርት ያደርጋሉ። የተጣራ ገቢ ማለት ግብሮች እና ተቀናሾች ከተቀነሱ በኋላ ያለው የእርስዎ ገቢ ነው።

- ***ብዙ ስራዎች ቢኖሩኝስ?*** ስምዎን እና ከእያንዳንዱ ስራ የሚገኘውን ገቢ በአዲስ መስመር ላይ በማስገባት እያንዳንዱን ስራ ለየብቻ ይዘርዝሩ። አስፈላጊ ከሆነ ተጨማሪ ወረቀት ይጨምሩ።
- ***እኔ በግል ተዳዳሪ ብሆንስ?*** ከንግድዎ የሚገኘውን ገቢ እንደ የተጣራ መጠን ይዘርዝሩ። ይህ የተጣራ መጠን የሚሰላው የንግድዎ ጠቅላላ የስራ ማስኬጃ ወጪዎችን ከጠቅላላ ደረሰኝ (ገቢ) በመቀነስ ነው። ጠቅላላ ደረሰኝ ወይም ገቢ ማለት ከሚቀርቡት ምርቶች ወይም አገልግሎቶች ሽያጭ የሚገኘው ገቢ በሙሉ ነው።

በ**ደረጃ 1** ውስጥ የተዘረዘረው ልጅ ገቢ ካለው፣ ***ደረጃ* 3 ክፍል B** ያሉትን መመሪያዎች ይከተሉ።

**3) ከሕዝብ እርዳታ/የልጆች ድጋፍ/በፍቺ ወይም በመለያየት ምክንያት የተፈቀደ የገንዘብ ድጋፍ የሚገኝ ገቢን ይዘርዝሩ።**
በማመልከቻው ላይ በ"ከሕዝብ እርዳታ/የልጆች ድጋፍ/በፍቺ ወይም በመለያየት ምክንያት የተፈቀደ የገንዘብ ድጋፍ" መስክ ላይ የሚመለከተውን ገቢ ይዘርዝሩ። <u>በገበታው ላይ ያልተዘረዘሩትን የማንኛውንም የህዝብ ዕርዳታ ጥቅማ ጥቅሞችን የገንዘብ ዋጋ ሪፖርት አያድርጉ</u>። ገቢው ከልጆች ድጋፍ ወይም በፍቺ ወይም በመለያየት ምክንያት ከተፈቀደ የገንዘብ ድጋፍ የተገኘ ከሆነ፣ በፍርድ ቤት የታዘዙ ክፍያዎችን ብቻ ሪፖርት ያድርጉ። መደበኛ ያልሆኑ ግን መደበኛ ክፍያዎች በሚቀጥለው ክፍል እንደ "ሌላ" ገቢ ሪፖርት መደረግ አለባቸው።

**4) ከጡረታ/ከሌሎች ሌሎች ገቢዎች የሚገኘውን ገቢ ይዘርዝሩ።**
በማመልከቻው ላይ በ"ጡረታ/ሁሉም ሌሎች ገቢዎች" መስክ ላይ የሚመለከተውን ሁሉንም ገቢ ይዘርዝሩ።

- ***በዚህ ምድብ ውስጥ ከብዙ ምንጮች ገቢ ብቀበልስ?*** ስምዎን እና ገቢዎን ከእያንዳንዱ ምንጭ በአዲስ መስመር ላይ በማስገባት እያንዳንዱን ምንጭ ለየብቻ ይዘርዝሩ። አስፈላጊ ከሆነ ተጨማሪ ወረቀት ይጨምሩ።

**5) አጠቃላይ የቤተሰብ ብዛት ይዘርዝሩ።**
በ"ጠቅላላ የቤተሰብ አባላት (ልጆች እና ጎልማሶች)" መስክ ውስጥ ጠቅላላ የቤተሰብ አባላትን ቁጥር ያስገቡ። ይህ ቁጥር በ**ደረጃ 1** እና **ደረጃ 3** ከተዘረዘሩት የቤተሰብ አባላት ቁጥር ጋር እኩል መሆን አለበት። በማመልከቻው ላይ ያልዘረዘሯቸው የቤተሰብ አባላት ካሉዎት፣ ወደ ኋላ ሄደው ያክሏቸው። ሁሉንም የቤተሰብ አባላት መዘርዘር በጣም አስፈላጊ ነው፣ ምክንያቱም የቤተሰብዎ መጠን ለነጻ እና ለቅናሽ ምግብ ብቁነትዎ ላይ ተጽእኖ ያሳድራል።

**6) የማህበራዊ ደህንነት ቁጥርዎን የመጨረሻዎቹን አራት አሃዞች ያስገቡ።**
አንድ አዋቂ የቤተሰብ አባል በተሰጠው ቦታ ላይ የማህበራዊ ደህንነት ቁጥራቸውን የመጨረሻዎቹን አራት አሃዞች ማስገባት አለባቸው። የማህበራዊ ዋስትና ቁጥር ባይኖርዎትም ለጥቅማጥቅሞች ለማመልከት ብቁ ነዎት። የትኛውም ጎልማሳ የቤተሰብ አባል የማህበራዊ ዋስትና ቁጥር ከሌለው፣ ይህንን ቦታ ባዶ ይተዉት እና "የማህበራዊ ዋስትና ቁጥር ከሌለ ምልክት ያድርጉ" በሚለው በቀኝ በኩል ባለው ሳጥን ላይ ምልክት ያድርጉ።

### 3.B በልጆች የተገኙ ገቢዎችን ይዘርዝሩ

**በልጆች የተገኙትን ወይም የተቀበሉትን ሁሉንም ገቢዎች ይዘርዝሩ።**
"የልጆች ገቢ" በሚለው ሣጥን ውስጥ ምልክት የተደረገባቸው በቤተሰብዎ ውስጥ ያሉ **ደረጃ 1** ውስጥ የተዘረዘሩትን የ<u>ሁሉም</u>ልጆች አጠቃላይ ገቢን ይዘርዝሩ። ለ*Foster Child* ከተቀረው ቤተሰብዎ ጋር አብረው እያመለከቱ ከሆነ ብቻ የእነርሱን ገቢ ይቁጠሩ።

- ***የልጅ ገቢ ምንድን ነው?*** የልጅ ገቢ ማለት በቀጥታ ለልጆችዎ የሚከፈል ከቤተሰብዎ ውጭ የተቀበሉት ገንዘብ ነው። ብዙ ቤተሰቦች ምንም አይነት የልጅ ገቢ የላቸውም።

## ደረጃ 4፡- የእውቂያ መረጃ እና የአዋቂ ፊርማ

***ሁሉም ማመልከቻዎች በአዋቂ የቤተሰቡ አባል መፈረም አለባቸው። ማመልከቻውን በመፈረም የቤተሰቡ አባል ሁሉም መረጃ በእውነት እና ሙሉ በሙሉ ሪፖርት እንደተደረገ ቃል እየገባ ነው። ይህን ክፍል ከማጠናቀቅዎ በፊት፣ እባክዎ በማመልከቻው ጀርባ ላይ ያሉትን መግለጫዎች ማንበብዎን ያረጋግጡ።***

| A) **የእውቂያ መረጃዎን ያቅርቡ።** ይህ መረጃ የሚገኝ ከሆነ የአሁኑን የፖስታ አድራሻዎን በተጠቀሱት መስኮች ላይ ይፃፉ። ቋሚ አድራሻ ከሌልዎት፣ ችግር የለውም። ስልክ ቁጥርን፣ የኢሜይል አድራሻን ወይም ሁለቱንም ማጋራት አማራጭ ነው፣ ግን እርስዎን ማግኘት ካስፈለገን በፍጥነት እንድናገኝዎት ይረዳናል። | B) **ስምዎን ያትሙ እና ይፈርሙ እና የዛሬውን ቀን ይፃፉ።** ማመልከቻውን የፈረመውን አዋቂ ስም ያትሙ እና ያ ሰው “የአዋቂዎች ፊርማ” በሚለው ሳጥን ውስጥ ይፈርማል። | C) **የተጠናቀቀውን ማመልከቻ ወደሚከተለው ይላኩ፡-**<br>Insert<br>School/District<br>address here |
|---|---|---|

## አማራጭ

**የልጆችን የዘር እና የጎሳ ማንነት ያጋሩ (አማራጭ)።** በማመልከቻው ጀርባ ላይ ስለልጆችዎ ዘር እና ጎሳ መረጃ እንዲያካፍሉ እንጠይቅዎታለን። ይህ መስክ አማራጭ ነው እና ለልጆችዎ ለነጻ ወይም ለቅናሽ ዋጋ የትምህርት ቤት ምግብ ብቁነት ላይ ለውጥ አያመጣም። ይህ መረጃ የተጠየቀው የግዛቱ የፌዴራል ሲቪል መብቶች ህጎችን ማክበርን ለማወቅ ዓላማ ብቻ ነው፣ እና የእርስዎ ምላሽ በማመልከቻዎ ከግምት መግባት ላይ ተጽዕኖ አያመጣም እና በግላዊነት ህግ ሊጠበቅ ይችላል። ይህንን መረጃ በማቅረብ፣ ይህ ፕሮግራም ከአድልዎ ነፃ በሆነ መልኩ መካሄዱን ለማረጋገጥ ይረዱናል።

**እባክዎ ማመልከቻውን በቀጥታ ወደ ልጅዎ ትምህርት ቤት ይመልሱ። የተጠናቀቁ ማመልከቻዎችን ወይም ጥያቄዎችን ወደ የዩናይትድ ስቴትስ የግብርና መምሪያ (United States Department of Agriculture, USDA) የሲቪል መብቶች ረዳት ፀሀፊ ቢሮ በፖስታ፣ በፋክስ ወይም በኢሜይል <u>አይላኩ</u> ወይም የልጅዎ የነጻ ወይም የቅናሽ ዋጋ ምግብ ብቁነት ይዘገያል።**